# ኖኅተ ምሥራቅ

ዮሐንስ ተክለሃይማኖት

አንቺ ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ . . . እንዳለ ቅዱስ ገብርኤል። እመቤታችንን ልዩ የሚያደርጓት ብዙ ዝርዝሮች ቢኖሩም ዛሬ ደግሞ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አንዱን እንመለከታለን። ጥበቡን ማስተዋሉን ይግለጥልን አሜን።

## በንጽሕናዋ ከፍጥረታት ሁሉ ልዩ ናት

መርገም በመብል ምክንያት ከመጣ በኋላ ከይሲ ሰይጣን አዳምና ሔዋንን የራሱ እንዲሆኑለት እንዲገዙለት ቃል አስገብቶ የደንጊያ ፊርማ በኮፒ አስፈርሞ አንዱን በሲኦል ሁለተኛውንም በዮርዳኖስ ቀብሮ ነበር። በዚህም ምክንያት ውሉደ አዳምና ሔዋን የዚህ የዕዳ ተገዥዎች ነበሩ። ደጋግ አባቶች እንኳ እግዚአብሔር በረድኤት ቢጎበኛቸውም ቢያነጋግራቸውም በተለያየ ምሣሌ በሚረዱት መልክ ቢገለጽላቸውም ያቺን የገነት በር አልፈው ሊገቡ አልቻሉም። ምክንያቱም የጥል ግድግዳው አልፈረሰም ነበርና። ስለዚህም እንዲህ እያሉ ይናገሩ ነበር "ጽድቃችን እንደ መርገም ጨርቅ ሆነ።"

ታዲያ ነቢያት አጋንንት በማህፀን ይቆራኙበት በነበረበት ወቅት እንዲህ በሚናገሩ በት ጊዜ፤ ጌታችን ከመወለዱ፣ ጸጋ በሙሉ ከመታደሉ በፊት፤ የእኛ እናት ድንግል ማርያም ምልዕተ ጸጋ እንደነበረች ሰማያዊው መልአክ ሲመሰክር "ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ደስ ይበልሽ" ብሏል

እንግዲህ ይህ የሚያሳየው የአዳምና የሔዋን መርገም እንዳልደረሰባት፣ ከተለዩ የተለየች፣ ከተቀደሱ የተቀደሰች፣ ከከበሩ የከበረች መሆኗን ነው። እግዚአብሔር ይስጥህ፤ ይስጥሽ የሚለው አነጋገር በእርግጥ ለፍጡራን ይገባል። ጸጋው ምሉዕ የሆነ የለምና እርሷ ግን ምስጋና ይግባትና ምልዕተ ጸጋ ናት። የሚጎድላት የለም። ታዲያ እንዲህ የሆነችው ገና ጌታችንን ከመፅነሷ በፊት፤ ይልቁንም በእናቷ በቅድስት ሐና ማህፀን ሳለች መንፈስ ቅዱስ ከልሎ (ጠብቆ) ስላቆያት ነው።

ነቢዩ ዳዊት ሲናገር "እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ፤ ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ። በጎነገርን የሚሠራ የለም. . . ።"(መዝ.፲፫(፲፬)፥፪-፫) ሁሉን አዋቂ እግዚአብሔር ሁሉን በሚመለከትበት ዓይኖቹ ተመለከተ። ሁሉም የዚያ የመርገም ፅዋ ቀማሾች ነበሩ። ታዲያ በዚያ ዘመን ምልዕተ ጸጋ መሆን እንዴት መለየት አይደለም? በእውነት ልዩ ናት እንጂ። ክፉ ጥንተ ጠላት ዲያብሎስ በግብር ልጆቹ ላይ አድሮ፤ እመቤታችንን(ምስጋና ይድረሳትና) መርገመ ሔዋን በብሥራተ ገብርኤል ጠፋላት እንጂ ደርሶባት ነበር ቢያስ ብሏ፤ በነዚህ ማሳረጃዎች ልናሳፍረው ይገባል።

ይኸ ደግሞ የጌታችንን ወደዚህ ዓለም መምጣት ክብርና ዋጋ ያቀለዋል። የአዳም መርገም በመላእክት የሚጠፋ አይደለም። በጥንተ ተፈጥሮ ሰውን የፈጠረ እግዚአብሔር ነውና፤ ዳግም በሐዲስ ተፈጥሮ ለመፍጠር ራሱ መምጣት አለበት እንጂ።አዳም ትእዛዝ በጣስ ጊዜ የረገመው አካላዊ ቃል ነውና፤ ሊያድነውም የሚችለው የእግዚአብሔር ቃል ነው እንጂ ፍጡር አይደለም።እነርሱ እንደሚሉት ቢሆንማ በብሥራተ መልአክ የፀነሱት የማኑሄም ሚስት እንዲሁም ካህኑ ዘካርያስና ቅድስት ኤልሳቤጥ፤ ከመርገመ አዳምና ሔዋን ነፃ በሆኑ ነበር።

እንኳን በመልአክ ብሥራት የፀነሱ ይቅርና፤ታዛዡ ይስ ሐቅን እንድትወልድ አጋዕዝተ ዓለም ሥላሴ ያበሠሯት የደጉ አብርሃም ባለቤት ሣራ እንኳ፤ መርገመ ሔዋን አልጠፋላትም። ስለዚህም ይህ አባባላቸው በቅዱስ መጽሐፍ ለመረመረው ክህደት ይሆንባቸዋል።የድኅነት መንገድም እንደጠፋባቸው ያሣያል። ነገረ ድኅነት፣ ነገረ ሃይማኖት እንዳልተገለጸላቸውም እንረዳለን። እኛስ እንዲህ አንልም መርገም (የጠፋው) በወልደ እግዚአብሔር እንጂ በፍጡር አይደለም አይሆንምም።

ደግሞስ የበደለው አዳምን የሚክሰው በሁሉም ነገር ሊበልጥና ሊለይ ይገባል። አዳምን ከሀቱም መሬት የፈጠረው አምላክ፤ ሊክሰው ሲመጣ ሀቱም፣ ድንግል፣ ፍፅምት፣ ንጽሕት ከሆነች ከእመቤታችን መወለድ አለበት እንጂ። መጀመሪያ ኃጢአት ከነበረባት ኋላ ከነጻች ተወለደ ማለት፤ ከቀዳማዊ አዳም ከፍጡሩ ሊያንስ አይደለምን? እንዲህስ ከሆነ ካሣ ከፋይ እንዴት ሊሆን ይችላል።

አዳም ጽድቅም ኃጢአትም የሚስማማው ሲሆን ከንጹሕ መሬት ከፈጠረው፤ ንጽሕና የባህርይ ገንዘቡ የሆነ አምላክ፣ ኃጢአት የማይስማማው ፈጣሪ፤ ሊያድነው ሲመጣ ኃጢአት ከነበረባት ሥጋ ተወለደ ማለት ስድብ አይደለምን? "በአንተና(በዲያብሎስና) በሴቲቱ(በድንግል ማርያም) መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ።" (ዘፍ.፫፥፲፭-፲፯) ብሎ ራሱ ባለቤቱ ያጸደቀው ጠላትነት ስላለ ይህ ይፈጸም ዘንድ ጠላት የማይገባን ነገር ይናገራል። እኛስ አባቶቻችን እንዳስተማሩን እንዲህ እንላለን።

"በአማን ነጸረ እግዚአብሔር አብ እምሰማይ ምሥራቀ ወምዕራበ፣ ሰሜነ ወደቡበ፣ ወውስተ ኩሉ አጽናፍ።አስተንፈሰ ወአጼነወ ወኢረከበ ዘከማኪ፤ ወሠምረ መዓዛ ዚአኪ፣ ወአፈቀረ ሥነኪ፣ ወፈነወ ኀቤኪ ወልዶ ዘያፈቅር።"

<u>ትርጉም</u> "እግዚአብሔር ከማደሪያው ከሰማይ ሆኖ ወደ ምዕራብ ወደ ምሥራቅ፣ ወደ ደቡብ ወደ ሰሜን፣በሁሉ አቅጣጫ ተመለከተ፣ ፈለገም። በንጽሕና የሚስማማውን አሸተተ፤ ዳሩ ግን እንዳንቺ ለእናትነት የበቃ ስላላገኘ፤ አንድ ልጁን ካንቺ ይወለድ ዘንድ ላከው።"እንዳለ አባሕርያቆስ /ቅዳሴ ማርያም/

ይኸንንም ነቢያት አስቀድመው ተናግረውታል። ለአብነት ነቢዩ ዳዊት የተናገረውን እንመለከታለን። "መሠረቶቿ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ እግዚአብሔር የጽዮንን ደጅ ይወዳል።" እንዳለ(መዝ.፹፮፥፩)ጥንት መሠረቷ ደጋግ ከሆኑ ቅዱሳን በሥጋ የተዛመዳት ሲሆን የወለዷትም ወላጆች ንጹሐን ክቡራን ነበሩ። የእርሷ ድንኳንነትም/እናትነትም/ ከያዕቆብ ወገኖች ከሆኑ ከቤተእሥራኤል ተለይታ በንጽሕናዋ የከበረች ስለሆነች እግዚአብሔር ከእርሷ ሊወለድ ንጽሕና መዓዛዋን እንዳሸተተ እንደወደደ ወድዶም እንደተወለደ ያስተምረናል።ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ ብሎም በተነፃፃሪነት ለማደሪያነት የተመረጠችው ድንግል ማርያም ከሁሉ በላይ እንደሆነች ያስረዳል። የእመቤታችን ንጽህናም ከፍጡራን የሚለይበትም እንደሚከተለው ይሆናል።

## የእርሷ የተፈጥሮ ንጽሕና በመሆኑ

ከዓለመ መላዕክት ብንነሳ፤ ምንም እንኳን ንጹሕ ሆነው ቢፈጠሩም በተሰጣቸው እግዚአብሔርን የማወቅ ኀሊና ተፈትነው ነበር። በፈተናው ያለፉ ቅዱሳን፣ ንጹሐን ሲባሉ። ያላለፉት ደግሞ ርኩሣን ተብለው ተጠርተዋል። ስለዚህ የእነርሱ በፈተና ያለፈ ንጽሕና ይባላል። የእመቤታችን ግን እንዲህ አይደለም። ከእናቷ ማኅፀን ጀምሮ መንፈስ ቅዱስ ከልሎ፣ ጠብቆ፣ አጽንቶ፣ ለያት። ብትባልም የእርሷ ያለፈተና በተፈጥሮ የጸና በመሆኑ ከመላእክትም ልዩ ያሰኛታል።

## ንፅህናዋ በውስጥም በአፍአም በመሆኑ ልዩ ናት

ከምድራውያን ጻድቃን እንጻር ብንመለከት ቅዱሳን ለታላቅ ማዕርግ የሚደርሱት ከብዙ ተጋድሎ በኋላ ነው ከእናታቸው ማኅፀን ጀምሮ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ያደረባቸው እንኳ ያንን ጸጋ አጽንተው ለመጠበቅ በትኅርምት፣ በጾም፣ በጸሎት፣

በተጋድሎ መትጋት አለባቸው። ከገቢር
ቢርቂ ከንግግር ይታገላሉ። ይህንንም
ሲያልፉ ከኀልዮ ለመራቅ ይጋደላሉ።
"ጻድቅ ሰባት ጊዜ ይወድቃል ሰባት ጊዜ
ይነሳል እንዳለ።

"እመቤታችን ግን ጠቢቡ ሰሎ
ሞን" ወዳጄ ሆይ ሁለን ተናሽ ውብነው።
ነውርም የለብሽም።" እንዳለ (መኃ.መኃ.
ዘሰሎ.፬÷፯) ሁለንተናዋ በውስጥም በው
ጭም ንጽሕት ናት፤ ነውር የተባለ የመ
ርገም ኃጢአት አልደረሰባትም። በዚህ
ብቸኛ ለመሆኗም ቅዱስ ገብርኤል የተና
ገረው ቃል ያረጋግጥልናል።

"ናዝሬት ገሊላ ወደምትባል አገር
ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብሔር
ዘንድ ተላከ" ብሎ እንደ እርሷ በው
ስጥ በአፍአ ንጹሕ የሆነ እንደሌለ፣ ከ
ፍጡር ተወዳዳሪ የሌላት ብቸኛ አንዲት
መሆኗን መስከረ። አንዳንዶች "ልበ ንጹ
ሐን ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን
ያዩታልና።"(ማቴ.፭÷፰) የሚለውን
ይዘው እኛም ንጹሕ መሆን እንችላለን
ይላሉ። እስኪ ከእመቤታችን ጋር እያነፃ
ፀርን እንየው። ሰዎች ለቅድሕና ማዕረግ
ለሚደረገው ብዙ ተጋድሎ እንዳላ
ቸው ከላይ ዘርዝረነዋል። ዳሩ ግን ከዚህ
ደረጃ የደረሱ እንኳ እግዚአብሔርን
በሚረዱት መልክ ምሣሌ ይገለጽላቸዋል
እንጂ፤ በመለኮታዊ ባህርይው የሚያ
የው የሚያውቀው የለም። ለዚህም ወን
ጌል ምስክር ናት።"መቼም ቢሆን እግዚ
አብሔርን ያየው አንድ ስንኳ የለም።
በአባቱ እቅፍ ያለ አንድ ልጅ እርሱ
ተረከው።" እንዳለ (ዮሐ.፩÷፲፰)

የእመቤታችን ንጽሕና ግን ያንን
ማንም ሊያየው እና ሊቀርበው የማይቻ
ለውን በከዊን፣ ምልአቱ ሳይከፈል
ወለደችው። ስለዚህ ከፍጡር ወገን ተን
ፃፃሪም የላትም። አስቀድሞም እግዚአብ
ሔር ለአገልጋዩ ለሙሴ ህጉን (ቃሉን)
ሲሰ ጠው፤ ለቃሉ መጻፊያ ሰሌዳ(ታቦት)
ያዘጋጅ ዘንድ እና ያንንም በውስጥ በአ
ፍአ በወርቅ እንዲለብጠው መመሪያ ሰጥ
ቶት ነበር።(ዘፀ.፳፭÷፲፩) ይኸውም ታቦቱ
የእመቤታችን ምሣሌ ነው። እርሷ የአካላዊ
ቃል ማደሪያ ሆናለችና። በውስጥም በው
ጪም በወርቅ መለበጡና ወርቅ ንጽሐ
ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ እንዲሁም ንጽሐ
ልቡናን ለመያዟ ምሣሌ ነው።

አንድም በውሰጥ በአፍአ ያለውን
ንጽሕናዋን ሲያሳየን ነው። ወርቅ በጥልቅ
መሬት ውስጥ ቢቀመጥ ከበላይ ያለውን
አፈር ቆፍረው በስተመጨረሻ ወርቁን
ቢያወጡት ያው ወርቅ ነው። ከበላይ የአ
ፈሩ መደራረብ ወርቅነቱን እንደማይለ
ውጠው እመቤታችንም ከአዳም ጀምሮ
የነበሩት የሥጋ ዘመዶቿ መርገም ቢደርስባ
ቸውም እርሷ ግን በአብራካቸው የነበረች
የምታበራ ዕንቁ ወርቅ ናት እንጂ ምንም
ምን የለባትም። ወርቅ እንደሚያብለጨ
ልጭ እርሷም ገና ሳትወለድ ለአበው ተስፋ
ሆና በሩቅ እየታየች ታበራ ነበር። ስለዚህ
ሥጋዊ ደማዊ አእምሮ እንዲህ ብሎ መና
ገር አይችልም። እንኳን የ፫ኛው ሺ ፍጡር
ይቅርና እነቅዱስ ኤፍሬምና አባ ሕርያቆስ
ስለ ንጽሕናዋ አመስግነው አልጠገቡም።

ስለዚህ በተአምረ ማርያም መቅ
ድም ላይ ሲነበብ እንደምንሰማው "ሥጋዊ
ነገር ከማሰብ መጠበቅ ከአዳም ልጆች
ለማን ተሰጠው? ኃጢአትን ከማሰብ መጠ
በቅ ለመላእክትስ እንኳን አልተቻላቸውም።
በቀደመው ወራት ያልተሰጣቸውን ሽተው
በድለው ከሰማይ ወደ ምድር ወርደዋ
ልና" በማለት እንዳደነቋት፤ እኛም በእ
ርሷ ንጽሕና ተከልለን ከዓለም ርኩሰትና
ከአጋንንት ፍላፃ እንድናለን። በረከቷ፣
ረድኤቷ ይደርብን። አሜን። ይሁንልን